# የግንቦት 7 ንቅናቄ እና የኦነግ ስብሰባ በ ቨርጅኒያ

በ አሉላ (alulla2@yahoo.com)

ዕሁድ ሐምሌ 3 ቀን 2003 ዓ.ም. (Sunday, July 10, 2011) በ ቨርጅኒያ ሸራተን ሆቴል የተካሄደውን ስብሰባ ተከታተልሁ። ስብሰባው ሦስት ድርጅቶችን ማለትም:- 1. ግንቦት 7 ለነፃነት ለፍትህና የእኩልነት ንቅናቄ 2. የኢትዮጵያ አንድነትና ፍትህ ንቅናቄና 3. የአፋር ሕዝብ ፓርቲን አጣምሬሃለው የሚለው ጥምረት ለነፃነት ለእኩልነትና ለፍትህ ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር በጋራ ያዘጋጁት መሆኑን የዕለቱ የስብሰባው መሪና የጥምረቱ ዋና ጸሐፊ መሆናቸውን ያሳወቁት አቶ ነዓምን ዘለቀ ገልጸዋል።

በግንቦት 7 ንቅናቄ፡ ኦነግና ኦብነግ መካከል በቅርቡ አብሮ በጋራ መሥራት በሚል የተለያዩ የሰሜን አሜሪካ ግዛቶችን በማካለል የሚካሄደውን ግልጽነትና ወጥነት የሌላቸውን ገለጻዎች በአካል በመገኘት ለማዳመጥና የታዳሚውን ስሜት ለመከታተል፡ እንዲሁም የሁለቱ ድርጅቶች ተወካዮች ምን ይላሉ ለሚለው ከራሴ ጆሮ በላይ ማመን በመቸገሬ ስብሰባውን ከጅምር እስከ ተጠናቀቀበት ሰዓት ተከታትያለሁ።

በዚህ ስብሰባ የተለመዱ መንደርደሪያዎችና በአንድ ዓረፍተ ነገር የሚጠቃለለውን ዋናውን መልዕክት ለማስተላለፍ በርካታ የንግግር "አበባዎችና ቃናዎች" ተወርውረዋል። በዚህ ስብሰባ ምን ተረዳን? ምን ተባለ? ለምን ተጨበጨበ? ታዳሚው ምን ይላል? የስብሰባው አካሄድ እንዴት ነበር? ውይይቶች ተካሄዱ ወይ? ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ አግኝተዋል? ይህ ስብስብ የሀገራችንንና የሕዝባችንን መሠረታዊ ችግሮች የተረዳና ለመፍትሄ የተዘጋጀ ነው? በቀጣይነት ይህ ስብስብ ሊደገፍ ወይስ ሊነቀፍ ይገባዋል? ለምን??? ወዘተ የሚሉት በአግባቡ መታየት ይኖርባቸዋል ከሚለው ግምቴ ባሻገር፡ በአንድ በኩል በወቅቱ በስብሰባው ቢገኙም አንዳንድ ታዳሚ ያላስተዋሏቸው ለኔ የታዩኝ፡ የተሰሙኝንና የገቡኝን ለማካፈል የትዝብት ብዕሬን ላነሳ ተገድጃለሁ። በሌላ በኩል በዚህ ስብሰባ ላይ በተለያየ ምክንያት ላልተገኙት በተለያየ ዓለም ክፍል ለተበተኑት ወገኖችና ለሀገር ቤት ወገኖች ሊያውቁት ይገባልና ከስብሰባው ባሻገር ልል የምፈልገውን እነሆኝ።

ስብሰባው የግንቦት 7 ንቅናቄን መሪ ዶር ብርሃኑ ነጋን በቀኝ፡ የኦነግን ሥራ አስፈጻሚ ዶር ኑር ደዴፎ በግራ አካቶ፡ በመሀል በራሳቸው አባባል "የፖለቲካ ፍላጎት የሌላቸውን" ዶር ጌታቸው በጋሻውን ያስቀመጠ ነበር። የዚህ ስብስባ ተጋባዥና የመጀመሪያ ተናጋሪ የትኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ሳልውክል ተገኘው ያሉት ዶር ጌታቸው በጋሻው ነበሩ።

በአቶ ነዓምን ዘለቀ የመድረክ መሪነት የተከፈተው ስብሰባ ዶር ጌታቸው በጋሻውን አስቀድሞ፡ የኦነግን ሥራ አስፈጻሚ አካል ዶር ኑር ደዴፎ አስከትሎ፡ ስለ አንድነት በሰበኩን ዶር ብርሃኑ ነጋ ገለጻ ተቋጭቶ ለጥያቄ አቅራቢ ታዳሚዎች ለያንዳንዳቸው ከሁለት ደቂቃ ያልበለጠ ጊዜ ተሰጥቶ ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል "ጥያቄና መልስ" ተካሂዷል።

የሦስቱን ተናጋሪዎች እያንዳንዳቸው ከወሰዱት ግማሽ ሰዓት ከሚጠጋ ንግግር ያስተላለፉት ዋና መልዕክት በአንድና ሁለት መስመር በማይበልጥ ይጠናቀቃል።

***ዶር ጌታቸው፣*** *"የኦሮሞ ሕዝብ መቶ በመቶ የአነግ ደጋፊ ነው"*

***ዶር ኑር፣*** *"የኦሮሞ ሕዝብና የመላው ኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ትብብር ወያኔን በማስወገድ ላይ ተመስርቶ፡ ወያኔ ከተወገደ በኋላ በሚመሰረት የሽግግር መንግሥት የኦሮሞ ሕዝብ የራሱን ዕድል ይወስናል"*

***ዶር ብርሃኑ፣*** *"የዜግነት መብት ካልተከበረ ኢትዮጵያዊነት አይኖርም፤ አንድነትም ትርጉም የለውም"*

*ይህ የሦስቱ ተናጋሪዎች ዋና መልዕክት ተያያዥነትና ተዛማጅነት ያለው ለሀገርና ሕዝብ እንዲሁም ለሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች የተወረወረ ነው። የወቅቱ ተናጋሪዎች ለተሰብሳቢው ያስደመጡት በመጠኑ የተቀረጠውን ንግግራቸውን በአንዳንድ ድረ ገጽ ማድመጥ ይቻላል። በስብሰባው ከተገኘው ታዳሚ የቀረቡ አስተያየቶችና ጥያቄዎች በአብዛኛው የስብሰባውን ምንነት ጠቋሚ ናቸው። የተሰጡትም አሳዛኝ፡ ትዕቢትንና ብልግናን የተላበሱ መልሶች ሌላው ሊያደምጣቸው በተገባ ነበር። ሆኖም ግን በውስጣቸው ያዘሉትን ሌላው እንዲያውቀውም፡ እንዲሰማውም አልተፈለገምና በዕለቱ በስብሰባው ላልተገኙ ወገኖች የታዘብኩትን አጋራለሁ።*

*የኢትዮጵያ ሀገራችንን የዘመናት ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት በትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን አካሄድና ዓላማ መገምገም፡ ጥሩ ሲሰሩ ማበረታታት፡ ሲሳሳቱ ስህተትን ጠቁሞ እርምት ውሰዱ ማለት ችሎታውና ዕውቀቱ ካላቸው ዜጎች ይጠበቃል። ኢትዮጵያ ከወያኔ ውድቀት በኋላ ዳግም የጥቂት እናውቅልሃለን ባዮች፡ እኛ ያልነው ብቻ ልክ፡ አካሄዶች አጥፊና ውድቀትን አስመዝጋቢ በመሆናቸው በቅድሚያ ሊጤኑና ሊታረሙ ይገባል።*

*የኦሮሞ ሕዝብ ትግል  የረዥም ጊዜ ታሪክ አለው። ሀገር የጥቂት ፈላጭ ቆራጮች፡ በዝባዦች፡ አምባገነኖች በመሆኗ የኦሮሞ ተወላጆች እንደ ኢትዮጵያዊነታቸው ለሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎች ታግለዋል። የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ መጐናጸፍ፡ የሕዝብ መንግሥት መመሥረት፡ የዜግነት መብት መከበር የአንድ ኢትዮጵያ ክፍል ወይም ክልል ጥያቄ ሳይሆን የሁሉም ዜጋ ጥያቄ ነው። ለዚህም ነው አደረጃጀትና የትግሉ ስልት ቢለያይም የጋራ ጥያቄያችንን በጋራ ለድል ለማብቃት የጋራ መድረክ አስፈላጊነት የሚወሳው።*

*የተናጋሪዎቹን ዋና መልዕክት አስመልክቶ፡* ***ዶር ብርሃኑ ነጋ ፣***

*ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷን ጠብቃ የኖረችው የዜጎች መብት ተከብሮ አይደለም። እየተረገጡም፡ እየተሰቃዩም፡ እየተገደሉም ሀገራቸውን ከባዕድ ወረራ እየተከላከሉ ቆይተዋል። የዜግነት መብቴ ካልተከበረ አላደርገውም ከተባለማ አድዋን በድል ባላጠናቀቅን፡ ዳግም በማይጨው ጦርነት (እሳቸው "ያፈርንበት ጦርነት" ያሉት) ኢጣሊያን ከአምስት ዓመት የጦርነት ዘመን እንዳያልፍ ባልተደረገ። እነኚህ የሀገርን አንድነት የማስከበር ታሪክ፡ መብትና*

ክብሩን ያጣው ኦሮሞ፡ ትግሬ፡ አማራ፡ ጉራጌ፡ ሀዲያ፡ ሱማሌው፡ አፋሩ፡ ሲዳማው፡ ወዘተ ታሪክ ነው። አንድነቱን የሚያናጋ፡ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈታተን ሲገጥመው ብሶቱንና ጭቆናውን ተሸክሞ ይዋደቃል። በደምና አጥንቱ ያስመዘገበውን ድል እንኳ ባንዳ ሲሾምበት

"ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" ብሎ የብሶቱን አዜመላት እንጂ ሀገሩን አልረገመም።

"ተሰቀለ ቢሉኝ ዝናሩ ነው ብዬ፡

ተሰቀለ ቢሉኝ ኮፍያው ነው ብዬ፡

ለካስ በላይ ሆኗል ታላቁ ሰውዬ"

እያለ የበላይንና የጀግኖች ልጆቹን ደምና አጥንት ከንቱ ያስቀሩትን ገዢዎች አፌዘባቸው እንጂ ኢትዮጵያን አልጠላም።

የፋሺስቱ ደርግ አረመኔያዊ አገዛዝ፡ ከየትኛውም አገዛዝ በከፋ መልኩ የሰው ልጅ ስብዕና የተረገጠበት የጭካኔ ዘመን እንኳ የሀገር መደፈርን ለድርድር ያላቀረበው ዜጋ ነው የሲያድ ባሬን የሶማሊያ ወረራ አሳፍሮ የመለሰው። በዚህ ዘመን ስለ ዜግነት መብት ሊታሰብ ከቶም አይቻልም ነበር። ፋሺዝም በነገሰባት ኢትዮጵያ እንኳ ሀገሩን፡ ታሪካዊ ቅርሱን፡ ባህሉን፡ ሃይማኖቱን፡ የማንነት መግለጫ ኢትዮጵያዊነቱን እየተንከባከበ ያለው ያ የዜግነት መብቱን ያጣው ትውልድ ነው። በዘመነ ወያኔና ሻቢያ ዕኩይ ተግባር የተጫረውን ወረራ ሆ! ብሎ የመከተው የዛሬው ጀግና ትውልድ ሀገሩን ብሎ ነው። የዜግነት መብቱን ከተመለከተማ ሀገር ብትወረር፡ ብትበጣጠስ፡ ዞር ብሎ ባላያትም። እነኚህ ሁላ የኢትዮጵያዊነት አንድነት፡ የግዛት ሉዓላዊነት መግለጫዎች ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያዊነት ማንነት መግለጫዎች ናቸው። የዜግነት መብትህ ካልተከበረ ኢትዮጵያዊነትህ ትርጉም የለውም አካሄድ አሳዛኝና አሳፋሪ ነው። የዜግነት መብት ገፋፊዋ ኢትዮጵያ አይደለችም። ኢትዮጵያዊነታችንን ከጥያቄ ሳናስገባ፡ ከመብት ጋር ሳናያይዝ በየጊዜው የተፈራረቁትን አፋኝና ጨቋኝ ሥርዓቶች እንደታገልን ሁላ፡ አሁንም ይህንን ዘረኛ አገዛዝ ከዚህ ዕይታ አንጻር ልንፋለመው ማስተማሩ ከተማሩ ይጠበቃል።

ዶር ብርሃኑ ይህንን ዋና መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ያደረጉት "ጥናታዊ ጽሁፍ (thisis)" እጅግ አስቂኝና ብዙ ሊባልበት ቢቻልም አድማጭ እራሱ የራሱን ግምት ይውሰድ ብያለሁ። ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር/ብሔረሰብ ሀገርነቷ በርካታ የተለያዩ ቋንቋዎች፡ ባህሎች (እሳቸው በነጠላ የተነተኑዋቸው አመጋገቦች፡ ሙዚቃዎች፡ አኗኗሮች፡ ወዘተ.)ና ዋና ዋና ሃይማኖቶቿ (እስልምናና ክርስትና)፡ ታሪካዊ ቅርሶቿ፡ የነፃነት ተጋድሏችን ወዘተ. የጋራ ታሪካችንና የኢትዮጵያዊነት ምንነት መገለጫዎቻችን ናቸው። የዶር ብርሃኑ የማንነት መገለጫ ፍልስፍናቸው በጥቅሉ "አክሱም ለኦሮሞው ምኑ ነው?" ከሚለው አባባል የዘለለ አይደለም።

*ዶር ኑር ደዴፎ፤*

የኦነግ የሥራ አስፈጻሚ አባል የሆኑት ዶር ኑር ደዴፎን ረጋ ባለ አነጋገራቸው ሊያስተላልፉ የፈለጉትን የድርጅታቸውን ዓላማ በግልጽና ዘና ባለ መልኩ አቅርበውታል። ዶር ኑር ዘና ብለው እንዲያቀርቡ የዳረጋቸውም በእኔ አመለካከት የዋሹት የለምና አልተደነጋገሩም። ወዲያና ወዲህ አልዘለሉም። ደግመው ደጋግመው ያስገነዘቡን "ወደፊት የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞ የኦሮሞ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ እንዲታይ" የሚል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቁጥር በመብለጡና ሁሉም ኦሮሞ የኦነግ ደጋፊ መሆኑን በጥያቄና መልስ ወቅት በተጨማሪ ያሳሰቡት የኦነግ ተወካይ፡ ሕዝበ ውሳኔ ቢሰጠን ቃሉን ባይገልጹትም እስከመገንጠል ሊሄዱ እንደሚችሉ የሚያግዳቸው ባለመኖሩ ይህንን እንቀበል ዘንዳ ወትውተዋል።

የአንድነት ኃይሉ የኦሮሞ ሕዝብ መብቱን ማግኘት አለበት ብሎ ሲታገል በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዴሞክራሲያና ለፍትህ ከሚካሄደው ትግል ጋር አጣምሮ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል። የኦነግን መገንጠል አለብን አቅዋም የአንድነት ኃይሉ ሲቃወም ከኦሮሞ ወገኖቹ ጋር በአንድነት መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት የለበትም። የኦነግን ኢትዮጵያዊ አይደለንም አካሄድ መቃወም የኦሮሞን ሕዝብ መቃወም አድርገው ሊወስዱ ከሚከጅላቸው አደናጋሪ ምሁራን መጠንቀቅ እጅጉን ይገባል። የኦነግን የመገንጠል አለብን አቅዋም የአንድነት ኃይሉ ሲቃወም፡ አሁንም ኦነግ አቅዋሙን ቀይሮ የጋራ የትግሉ አጋር እንዲሆን ከመጣር መቆጠብ የለባቸውም።

በተደጋጋሚ እንደተገለጸው በአሁኑ ወቅት ኦነግ ላይ ያለው ጥያቄና ከሚከተለው መስመር ጋር ብዙዎች የኦነግን አካሄድ የምንቃወምበት ምክንያት ከዚህ በፊት በ1983 የሎንደኑ ጉባዔ በወያኔ ሻቢያና አሜሪካ "የሰላም ጉባዔ" ላይ በድጋፍ ሰጪነት በመገኘትና በሽግግሩም ወቅት የተከሰቱት በበደኖ፡ አርባ ጉጉ፡ አሶሳ ፍጅቶች ለድርጅቱ ያመጡት ውጤት ጉዳት መሆኑ እየታወቀ አሁንም በሻቢያ ጉያ ታቅፎ በሻቢያ ፀረ-ኢትዮጵያዊነትና ፀረ-አንድነት ተግባር እራሱን ከማሰለፍ መቆጠብ ይኖርበታል በማለት ነው። በአሁኑ ወቅትም የተያዘው ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን አግልሎ የሚካሄድ ግልጽነት የሌለው የአንድ ወገን ስብስብ አደገኝነቱን በመገንዘብ ጭምር ነው። አንድ የኦሮሞ ተወላጅ አስተያየት ሰጪ የተሰብሳቢውን ቀልብ እንደሳቡት "ከአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚበዛ ቁጥር ያለው የኦሮሞ ሕዝብ ከሆነና የኦሮሞ ሕዝብ ደግሞ መቶ በመቶ የኦነግ ደጋፊ ከሆነ፡ ኦነግ ለምን ለሌሎቻችን ጭቁን ሕዝቦች መብት ሁሉ ታግሎ ሁላችንንም ነፃ አያወጣንም። ለምን ኦሮሚያን እገነጥላለው ከሚል፡ ኢትዮጵያን ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ አይገነጥልልንም። ለምን ኢትዮጵያን ከድህነት፡ ከድንቁርና፡ ከበሽታ ገንጥሎልን የሁሉም ዜጎቿ የሆነችዋን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት አይታገልልንም?"። ሥርዝ የተጨመረበት። የስበባው መደምደሚያና የታዳሚውን ስሜት የሳበና የኮረኮረ ውብ አባባል ለግንቦት 7 መሪና ለኦነግ መሪዎች ዋናው የጥሪ መልዕክት ሊሆን ይገባዋል። በጥቅሉ ስብሰባው የተቋጨው ታዳሚው አንድነታችንን አታናጉ፡ ኢትዮጵያዊነታችን ለድርድር አይቀርብም፡ በሚል መልስ የሌለው ጥያቄ የታጀበ ለመሆኑ ቢያንስ 600 ጆሮ አድምጦታል።

ሌላው የዶር ኑር ተደጋጋሚ ማሳሰቢያ "ሕዝብ ይወስናል" የሚለው ለራሳቸው የገባቸው ለሌላው ግን "ግልጽ ያልሆነ" የመሰላቸው አባባል ነው። ለዚህ ተደጋጋሚ አባባላቸው ድጋሚ እንዲታወቅ የሚገባው እርሳቸው እንደሚሉትና ሁሉም እንደሚስማማበት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በማምጣት የዜጎች ያልተገደበ መብት ተከብሮ፡ የሕግ የበላይነት ለማስፈን ከሆነ ትግሉ፡ ለዚህም ኦነግ የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ዘረኛውን የወያኔን መንግሥት አስወግዶ ኢትዮጵያን የልጆቿና የሁሉም ዜጎቿ ለማድረግ ከሆነ ጥረቱ፡ ኦነግም ከኦሮሞ ልጆቹና ከሌሎች ወገኖቹ ጋር በጋራ የድሉን ፍሬ መቋደስ ሲገባው "ሕዝብ የሚወስነው ምኑን ነው?" የሚል ጥያቄ ቢያስነሳ አግባብነት ይኖረዋል። ኦነግ ከወያኔ ውድቀት በኋላ በሚመሰረተው የሽግግር መንግሥት ተካፋይ በመሆን የሀገሪቷንና የሕዝባችንን መሠረታዊና መጠነ ሰፊ ችግሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ቁርጠኝነቱ ካለው፡ የኦነግ ጠላት እንደሌላው ሕዝብ፡ አፋኝ፡ አምባገነን፡ ዘረኛ አገዛዞች ከሆኑና በነኚህ መቃብር ላይ መብቱን ካስከበረ መገንጠልን እንደ መፍትሄ ለምን ይወስደዋል? የኦነግ ጠላት በየጊዜው የተፈጠሩት አገዛዞች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ወይም የሌላ አንድ ብሔረሰብ ዘር ከሆነ ጥያቄውም አፈታቱም ሌላ ነው። በአጠቃላይ ኦነግ ዕውነት ለኦሮም ሕዝብ መብት ከቆመ፡ በመሰል መልኩ ከተደራጁ የአንድ ብሔርና ኅብረ ብሔር አካላትና ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመምከር የማንንም ፈቃድ ሳይጠይቅ መዘጋጀት ይኖርበታል። ኦነግ በዚህ መልኩ ዝግጁነቱን ካሳየ የመላውን ሕዝባችንን መብት አስከብሮ ወያኔ ለሀገራችን የተመኘውን መበታተንና መከፋፈል በመቋቋምና ብሎም በማስወገድ ደረጃ ዋናውን ሚና ሊጫወት እንደሚችል ጥርጣሬ ሊገባው አይገባም።

*ዶር ጌታቸው በጋሻው፡*

ወያኔ በየዓመቱ አስመዘገብኩ የሚለውን የተሳሳተ ዓመታዊ ዕድገት ሥሌት፡ ካላቸው ቀጥተኛ ሙያ አንጻር ልክ እንዳልሆነ ሲጽፉ፡ በተለያየ መገናኛ ሲያስረዱ ለአንባቢያቸውና ለአድማጮቻቸው እውነተኛነቱን ለማስረገጥ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን (እንደ WHO, UNDP, UNCHR ወዘተ.) ዘገባ በማጣቀስ ስታስቲክሳዊ ስሌት የሚሰጡት ዶር ጌታቸው በአንድ አገር ወዳድ ጸሐፊ የቀረበውን ጽሁፍና የጥቂት ጓደኞቻቸውን ምስክርነት ይዘው"የኦሮሞ ሕዝብ መቶ በመቶ የኦነግ ደጋፊ ነው" ስሌት ሲያስደምጡን የፈለጉት አካሄድ ይሳካላቸው ዘንድ ምንም ከማለት እንደማይመለሱ ያስገምታል ቢባል ስድብ አይባልም።

ዶር ጌታቸው ሊያጥላሉት የፈለጉትን የአንድነት ኃይል ከማንም በላይ ችግሩን ሊረዱና ሊስተካከል የሚችልበት መንገድ ላይ አስተዋጽዎ አድርገው በጋራ የኦነግንና የኦብነግን ችግር ትልቅ ነው ትንሽ፡ ሕጋዊ ነው ሕገ ወጥ፡ በሰላም ነው በሁለገብ፡ ሳይለይ ተቃዋሚው ኃይል ይመክርበት ዘንድ ጥረት ቢያደርጉ ምስጋና በጎረፈላቸው። ኦነግን ከግንቦት 7 በስተጀርባውም ሻቢያ መኖሩን እየተረዱ ሌሎችን አግላይ የሆነ ፖለቲካ አደገኛነቱን ሊረዱ ከተሳናቸው ችግር ያለባቸው ይመስለኛል። ስለአንድነት ሊሰሙም የፈልጉ አይመስሉም፡ ቢያዙትም ጎዳና እንዲተቹ ሁሉ አለመፈለጋቸውን "አንዳንድ ተቺዎች" በማለት የያዝኩት ጎዳና ብቻ ነው አዋጭ በማለት ማቃለል ከማንም በላይ እራሳቸውን ሊጎዳቸው እንድሚችል በመገንዘብ ቆም ብለው ቢያስቡበት ላሳስብ እወዳለሁ።

በዚህ ስብሰባ ሌላው ዋነኛው መደመጥ የሚገባው ከታዳሚው የቀረበው ጥያቄና መልስ ነበር። ከአንድ ታዳሚ የቀረበ ጥያቄ ጭብጡ እንዲህ ይላል “ጥያቄዬ ለዶር ብርሃኑ ነው፡ አሁን ማለትም በግንቦት 7 ንቅናቄ፡ በኦነግና ኦብነግ መካከል የተጀመረው በጋራ መምከር ጥሩ ነው ብዬ ልቀበል፡ ሆኖም ግና ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች አልተካተቱም። በመሆኑም በናንተ በኩል ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ለመወያየትና በጋራ ለመሥራት ለመምከር ዝግጁ ናችሁ ወይ? ለዚህ ደግሞ ካስፈለገ ነጻ የሆኑ አካሎች (እኔ እራሴ የማውቀው አለ) ለማወያየትና ምክክር ይደረግበት ዘንድ ለማግባባት ፈቃደኞች ናቸውና በዚህ በኩል ምን ትላላችሁ?”

ዶር ብርሃኑ በመረረና በኃይለኛ አነጋገር “እኛ አሁን ያለነው ትግል ላይ ነው፡ የምን ውይይት፡ የምን ምክክር። በውይይትና በምክክር ጊዜ የምናቃጥልበት ወቅት ላይ አይደለንም። ደግሞ ከማን ጋር ነው የምንወያየው? የምንነጋገረውም አካል የለም።”

ይህ ነው እንግዲህ በሀገራችን ኢትዮጵያ በውይይት፡ በንግግር፡ በልዩነት፡ ሀሳብን በነጻ በመግለጽ ሊገነባ ለሚፈለገው ዴሞክራሲያዊ ግንባታ ቋሚ ጠበቃነኝ ከሚሉ መሪ የተሰጠው መልስ። ዶር ብርሃኑ ከጅምር ንግግራቸው ጀምሮ ለጥያቄዎች በሚሰጡት መልስ ስደተኛ መሆናቸውን ሁላ የዘነጉና ቤተ-መንግሥት ያሉ መሪ አድርገው እራሳቸውን ያስቀመጡ ይመስሉ ነበር። ወይም ቀጣይ የመለስ ተኪ ከኔ በላይ ላሳር ያሉ ይመስላሉ። እንግዲህ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች፡ በተለይ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር የሀገራችንንና የሕዝባችንን ችግሮች ለመፍታት የበኩላችሁን ጥረት የምታደርጉ ሁላ ያላችሁን ልዩነታችሁን እንደያዛችሁ ለሀገርና ለሕዝብ ስትሉ ቂምና ጥላቻን አስወግዳችሁ ልትተባበሩ ካልተዘጋጃችሁ፤ እየተደገሰ ላለው የጥፋት ጎዳና በታሪክ ከተባባሪነት ጎራ መመደባችሁ አይቀርምና፡ በታሪክና በትውልድ ላለመወቀስ ተነሱ። ተዘጋጁ።

ሌላው አንድ ጠያቂ ያቀረቡት ጥያቄና የተሰጠው አሳፋሪ የብልግና መልስ እነሆ፡

ጠያቂ፡ “…እናንተ አንድ ቋንቋ፡ አንድ ሀገር፡ አንድ ሃይማኖት ብቻ ብላችሁ ስትነሱ የሌላውን የኅብረተሰብ ክፍል ቋንቋና የተለየ ሃይማኖት ከምን ግምት ወስዳችሁ ነው?…”

መልስ ዶር ብርሃኑ ነጋ፡ “እኛ አንድ ቋንቋ ብቻ ይኑር የሚል አባባል አላልንም፡ እኛ አንድ ሃይማኖት ብቻ አላልንም፡ ጠያቂው ይህንን ከየት እንዳመጡት አይገባኝም። እንዲህ የሚያስቡ ካሉ አዕምሮአቸው (ጭንቅላታቸው) <u>በንፍጥ</u> የተሞላ ነው።” ሥርዝ የተጨመረበት።

ዶር ብርሃኑ በዚህ የብልግና አነጋገራቸው፡ ስድብ ጎረቤቱ ከሆነው መለስ ቢመሳሰሉና ቢተቹ ያስጮሃልን? የአንድ ፖለቲካ ድርጅት መሪና ሀገርን ሕዝብ ለመረጠው አመራር ሊያስረክቡ የሚታገሉ ምሁር የፈለገ ዓይነት፡ የተሳሳተም ጥያቄ ቢቀርብላቸው የዚህ ዓይነት ተራ ብልግና ከአንደበታቸው መውጣት አለበትን? እነዚህንና ሌሎችን የዶር ብርሃኑን ትዕቢትና ንቀት የተሞላበት አነጋገሮች እየተመነዘሩ ቢፃፉ ጥፋት ነውን? ለዚህ ነው እንግዲህ መጀመሪያው ላይ እንደገለጽኩት ከታዳሚው የቀረቡት አስተያየቶች፡ ጥያቄና መልሶች ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል እንዳያደምጣቸው የተቆለፉት።

ውድ ወገኖች፡

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ከመቼውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ ስቃይና መከራው ቀጥሏል። ረሃብና ድርቅ በአሳሳቢ ሁኔታ በሀገሪቷ መከሰቱን የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እያሳሰቡ ነው። ችግር ያልተለየው አርሶ አደር ገበሬ ከመሬቱ እየተፈናቀለ እየተወረወረ ነው። ለም መሬታችን ለባዕዳን እየተቸበቸበ ነው። በልማት ስም የተፈጥሮ ደናችን እየተጨፈጨፈ ነው። የትኛውም አካባቢ እየተከሰተ ያለው የመብራትና የውኃ እጦት የሕዝባችን መለስተኛ የዕለት ተለት ኑሮ መከራውንና ችግሩን እያባባሱት ነው። የዋጋ ግሽበቱ በአስከፊ ሁኔታ እየጨመረ ነው። ሕዝባችን ግራ እተጋባበት አስከፊ ደረጃ ላይ ይገኛል። ሰሞኑን በተያዘው አዲስ የገቢ ግብር ማሰባሰብ ዕቅድ እጅግ በማይታመን ሁኔታ ከትንንሽ ሱቅ በደረቴዎች ጀምሮ እንዲከፍሉ የሚበየንባቸው ግብር እጅግ ዘግናኝ ከመሆኑ የተነሳ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል አይታወቅም። በዓመት አይደለም በ10 ዓመት ሊከፍሉ የማይችሉት የቀረጥ ግብር እያስደነገጣቸው የዕለት ጉሮሯቸውን መሸፈኛ አነስተኛ ንግዳቸውን ሊዘጉ የተገደዱ በርካታዎች ናቸው። በጥቅሉ በሀገራችን እጅግ የተጠራቀመና የተወጠረ ችግር በማንኛውም ጊዜ ያለማንም አነሳሽነት ሊፈነዳ እንደሚችል ከገመትን ዘንዳ፡ የሚነሳው ማዕበል ለጥፋት የተዘጋጁ ኃይሎች እጅ እንዳይወድቅ ተዘጋጅቶ መገኘት መታሰብ ያለበት አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን መጥቀም ግድ ይላል።

በግንቦት 7 ንቅናቄ፡ ኦነግና ኦብነግ መካከል የተጀመረው አግላይ ስብስብ እራሳችሁ ልትመክሩበትና ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ በመረዳት ለእርምት ልትዘጋጁ ይገባል። ይህ የጥሪ ደወል አልሰማ ካላችሁ ሀገርና ሕዝብ እንደሚያሳፍራችሁ ጥርጣሬ አይግባችሁ። ሁሉም መብቱንና ሀገሩን ያጣው ሕዝብ ያነጣጠረው አጥፊዎች፡ ዘረኞችና ከፋፋዮች ላይ መሆኑን ተገንዝባችሁ ትክክለኛውን መስመር ለመከተል ድፍረቱ ሊኖራችሁ ይገባል። ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፡ የሲቪክ ማህበራት፡ ታዋቂ ግለሰቦች፡ ወጣቶች፡ ሴቶች እህቶቻችን፡ ምሁራን የሃይማኖት አባቶች በሞላ ሀገርና ሕዝብ የተደቀነባቸውን አስከፊ አደጋ በጋራ ለመመከትና ኢትዮጵያን ለአንዴም ለመጨረሻም በልጆቿ ለልጆቿ ለማድረግ መዘጋጀት የዜግነት ግዴታችን ነውና ለወሳኙ ፍልሚያ እንነሳ።

ኢትዮጵያዊነት የማንነታችን መግለጫ ነው!!!

የኢትዮጵያ አንድነት በልጆቿ ተከብሮ ይኖራል!!!

ቸር ይግጠመን

አሉላ (alulla2@yahoo.com)

ሐምሌ 14 ቀን 2003 ዓ.ም. (July 21, 2011)